MedStar Health

*የሚጸናበት ቀን፡- Oct. 1, 2009*
*የተሻሻለበት ቀን፡- Sept. 15, 2017*

# የMedStar Health Inc.
## *የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ*

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የተመለከተ የህክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና ለሌሎች ይፋ እንደሚደረግ እንዲሁም እርስዎ ይሄንን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።

## ይህን ማስታወቂያ ማን ይከተለዋል

MedStar Health Inc. እና ተባባሪ ተቋማቱ እንዲሁም ቅርንጫፎቹ የተለያዩ ሕጋዊ ተቋማት ናቸው። ሆኖም ግን፣ በጋራ ባለቤትነት እና ቁጥጥር ስር ናቸው፣ እናም ለ HIPAA የግላዊነት ደንብ ዓላማዎች እራሳቸውን እንደ አንድ **ሽፋን ያለው ተባባሪ ተቋም (ACE)** አድርገው አደራጅተዋል። ይህ ሁኔታ MedStar፣ ተባባሪ ተቋማቱ እና ቅርንጫፎቹ አንድ የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያን እንዲይዙ ይፈቅድላቸዋል። ይህ ማስታወቂያ የMedStar ድርጅት የጤና መረጃ አሰራሮችን ይገልጻል። ሁሉም ተቋማት፣ ጣቢያዎች እና አካባቢዎች የዚህን ማስታወቂያ ደንቦች ይከተላሉ። በተጨማሪም፣ በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተገለጸው እነዚህ ተቋማት፣ ጣቢያዎች እና አካባቢዎች ለሕክምና፣ ለክፍያና ለጤና እንክብካቤ ክወናዎች እርስ በርሳቸው የሕክምና መረጃ ሊጋሩ ይችላሉ።

## ለእርስዎ ያለብን ግዴታ

የህክምና መረጃዎን ግላዊነት ቅድሚያ-ለታካሚ የሚለው ቃል-ኪዳናችን ወሳኝ ክፍል አድርገን ዋጋ እንሰጠዋለን። የታካሚ ግላዊነት ጥበቃን ሰዎችን በመንከባከብ እና ጤናን በማሻሻል የታመነ መሪ የመሆን ራዕያችን እና ታካሚዎቻችንን የማገልገል ተልዕኳችን ወሳኝ አካል አድርገን እናየዋለን። በዚህ የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ (“ማስታወቂያ”) ውስጥ ለተገለጹት አላማዎች አስፈላጊ የሆነውን የጤና መረጃዎን አነስተኛ መጠን ብቻ ለመጠቀም እንጥራለን።

ከእርስዎ መረጃ የምንሰበስብ ሲሆን፣ መረጃውን ጥራት ያለው እንክብካቤን ለእርስዎ ለማቅረብ እና የተወሰኑ ህጋዊ መስፈርቶችን ለማሟላት እንጠቀምበታለን። የእርስዎን የጤና መረጃ በምስጢር እንድንጠብቅ፣ እንዲሁም የእኛን ህጋዊ ግዴታዎች፣ የግላዊነት አሰራራችንን እና የእርስዎን መብቶች የሚገልጸውን ይህን ማስታወቂያ እንድንሰጥ በሕግ እንገደዳለን። በጣም ወቅታዊ የሆነው ማስታወቂያችንን ደንቦች መከተል ይጠበቅብናል። አገልግሎቶችን እንዲፈጽሙልን ለሌሎች ሰዎች እና ኩባንያዎች መረጃ ስንሰጥ፣ ግላዊነትዎን እንዲጠብቁ እንጠይቃለን።
ከአእምሮ ጤንነት፣ ከአልኮል እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆች፣ እንዲሁም ከተላላፊ በሽታዎች ወይም ከሌሎች የጤና ችግሮች የተገናኙ ሕጎችን የመሳሰሉ፣ ተጨማሪ ጥበቃዎችን ሊሰጡ የሚችሉ የምንከተላቸው ሌሎች ሕጎች አሉ።

ይህ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ጣቢያዎች እና ሰዎች ይሸፍናል፡- ወደ ማህደርዎ መረጃ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ሁሉንም የጤና ባለሙያዎች፣ እዚህ እያሉ እርስዎን እንዲያግዙ የተፈቀደላቸው ሁሉንም የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች፣ ሁሉንም ተባባሪዎቻችን እና በጣቢያ ላይ ያሉ ተቋራጮችን፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም መምሪያዎች እና ክፍሎች፣ ሁሉንም የጤና እንክብካቤ ተማሪዎች፣ በ MedStar ስርዓት ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና አቅራቢዎች፣ እንዲሁም በዚህ ጣቢያ ላይ ሆነው እንክብካቤ በመስጠት ላይ ያሉ የግል ሀኪምዎን እና ሌሎች። የእርስዎ ሐኪም በእርሱ ወይም በእርሷ የግል ቢሮ ወይም ክሊኒክ ውስጥ የተፈጠረን የጤና መረጃ አስመልክቶ የተለዩ ፖሊሲዎች ወይም ማስታወቂያዎች ሊኖራቸው ይችላል።

©2017 MedStar Health, Inc.

**የጤና መረጃን እንዴት ልንጠቀምና አሳልፈን ልንሰጥ እንደምንችል**

**ሕክምና፡-** የጤና መረጃዎን ሕክምና ወይም አገልግሎት ለማቅረብ፣ የጤና እንክብካቤዎን ለማስተባበር ወይም ለማስተዳደር ወይም ለሕክምና ምክር ወይም ሪፈራሎች ልንጠቀምበት እና አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። በዶክተሮች፣ ነርሶች፣ ቴክኒሻኖች፣ የሕክምና ተማሪዎች እና በተቋሞቻችን ውስጥ ለእርስዎ እንክብካቤ ለሚያደርጉ ሌሎች ሰራተኞች ወይም ከተቋሞቻችን ውጭ ካሉ መሰል ሰዎች ጋር የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እና አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።እንደ ማዘዣዎች፣ የላብራቶሪ ስራ እና ራጂዎች ያሉ የሚያስፈልግዎትን የተለያዩ አገልግሎቶች ለማስተባበር የእርስዎን መረጃ ልንጠቀም ወይም ልናጋራ እንችላለን። እኛ ከወጡ በኋላ እንደ የቤተሰብ አባላት፣ የቤት የጤና ኤጀንሲዎች፣ ቴራፒስቶች፣ የአረጋውያን ማእከላት፣ ቀሳውስት፣ እና ሌሎችም በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ መሳተፍ የሚችሉ ከተቋማችን ውጪ ላሉ ሰዎች ስለ እርስዎ መረጃዎችን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ለእርስዎ የጤና እቅድ ወይም ለሌላ አገልግሎት ሰጪ ሪፈራል ወይም ምክክር ለማመቻቸት መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

**ክፍያ፡-** ለቀረቡ አገልግሎቶች እና ህክምና ክፍያ መቀበል እንድንችል መረጃዎን ልንጠቀም ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ይህንን መረጃ ከመድህን ሽፋን ኩባንያዎ ወይም የክፍያ መረጃን ለመካወን ጥቅም ላይ ከዋለ ሶስተኛ ወገን ጋር ልንጋራ እንችላለን። (ከዚህ በታች እንደተገለፀው፣ ለጤና አገልግሎትዎ ሙሉውን እና ከኪስዎ የሚከፍሉ ከሆነ፣ ለኢንሹራንስ ኩባንያዎ መረጃዎን እንዳናጋራ ሊጠይቁ ይችላሉ።) እርስዎ ምን ጥቅሞች ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ለማረጋገጥ፣ የቅድሚያ ፈቃድ ለማግኘት እና ስለ ህክምናዎ በመንገር ለእንክብካቤዎ መክፈላቸውን ለማረጋገጥ የመድህን ሽፋን ኩባንያዎን ልናነጋግር እንችላለን። እንደ የቤተሰብ አባሎች ላሉ የክፍያ ሀላፊነት ሊኖርባቸው ለሚችሉ ወይም ለሚከፍሉዎ ሶስተኛ ወገኖች መረጃ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። እንደ የክፍያ ኩባንያዎች፣ የይገባኛል ጥያቄዎችን የሚያካሂዱ ኩባንያዎች እና ሰብሳቢ ኩባንያዎች ለመሳሰሉ የክፍያዎች ሂደትን እንድናከናውን ለሚያግዙን ሶስተኛ ወገኖች መረጃ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የጤና እንክብካቤ ክወናዎች፡-** አገልግሎታችንን ለማከናወን እና ሁሉም ታካሚዎቻችን ጥራት ያለው እንክብካቤ እንደደረሳቸው ለማረጋገጥ የጤና መረጃዎን እንደ አስፈላጊነቱ ልንጠቀምበት እና አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ያገኟቸውን አገልግሎቶች ጥራት ወይም እርስዎን በመንከባከብ ረገድ የሠራተኞቻችንን አፈጻጸም ለመገምገም የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። የጤና አገልግሎታችንን ለማሻሻል ወይም እንክብካቤን ለማቅረብ የተሻሉ መንገዶችን ለማግኘት የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። የጤና ሰራተኛ ልዩ መብቶችን ለመስጠት ወይም የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎቻችንን ብቃት ለመገምገም የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። ምን አይነት ተጨማሪ አገልግሎቶችን ማቅረብ እንደሚኖርብን እና አዳዲስ ህክምናዎች ውጤታማ እንደሆኑ ለመወሰን የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እንችላለን። ለግምገማና ለትምህርት አላማዎች ለተማሪዎች እና ባለሙያዎች መረጃ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። እንዴት እየሠራን እንዳለን ለማነፃፀር እና የት ቦታ ላይ ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደምንችል ለመመልከት የእኛን የጤና መረጃ ከሌሎች የህክምና ተቋማት መረጃ ጋር ልናጣምር እንችላለን። የጤና መረጃን ለቢዝነስ እቅድ ልንጠቀም ወይም ህጉን እያከበርን መሆናችንን ለማረጋገጥ ለጠበቃዎች፣ ለሂሳብ ሠራተኞች፣ ለአማካሪዎች እና ለሌሎች አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ሌሎች እርስዎ ማን እንደሆኑ ሳያውቁ የጤና እንክብካቤ እና የጤና እንክብካቤ አሰጣጥ ለማጥናት የማንነቱ-ያልተለየውን መረጃ መጠቀም እንዲችሉ፣ እርስዎን የሚለይ የጤና መረጃን ልናስወግድ እንችላለን። እንደ አንድ የጤና እቅድ እየከወንን ከሆነ፣ ለጋራ እቅድ ሽፋን ብቁነትን ለመወሰን ዓላማዎች የዘረመል መረጃን አንጠቀምም ወይም አሳልፈን አንሰጥም (ይህ የረጅም ጊዜ የእንክብካቤ እቅዶችን አይመለከትም)።

**የቢዝነስ ተባባሪዎች፡-** ከቢዝነስ ተባባሪዎች ጋር ባሉ ኮንትራቶች አማካኝነት በMedStar Health የሚሰጡ አንዳንድ አገልግሎቶች አሉ። ምሳሌዎች፣ የእርስዎን የጤና መዝገብ ቅጂ ስንሰራ የምንጠቀምበት የቅጂት አገልግሎት፣ አማካሪዎች፣ የሒሳብ ባለሙያዎች፣ ጠበቃዎች፣ የሕክምና ትራንስክሪፕተሮች እና የሶስተኛ ወገኖች የክፍያ ኩባንያዎችን ያካትታሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ኮንትራት በሚሰጡበት ጊዜ፣ የጠየቅናቸውን ስራ ማከናወን እንዲችሉ የጤና መረጃዎን ለቢዝነስ ተባባሪዎቻችን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ሆኖም ግን፣ የጤና መረጃዎን ለመጠበቅ፣ የቢዝነስ ተባባሪዎቻችን መረጃዎን በአግባቡ እንዲጠብቁ እንጠይቃለን።

©2017 MedStar Health, Inc.

**አንዳንድ የማርኬቲንግ እንቅስቃሴዎች፡-** የመሸጫ ዋጋ የማስተዋወቂያ ስጦታዎችን ለማስተላለፍ፣ በ MedStar Health ስለሚሰጡ ምርቶች፣ አገልግሎቶች እና የትምህርት ፕሮግራሞች ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት፣ ስለ ጉዳይ አስተዳደር እና እንክብካቤ ማስተባበር ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት እና ስለ ሕክምና አማራጮች ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር የሕክምና መረጃዎን ልንጠቀም እንችላለን። እርስዎ ይህን እንድናደርግ በመፍቀድ የስምምነት መስጫ ካልፈረሙ በስተቀር፣ እኛ ለማንኛውም ሶስተኛ ወገን፣ ለገበያ እንቅስቃሴዎቻቸው፣ የእርስዎን የጤና መረጃ አንሸጥም።

**የጤና መረጃ ልውውጦች፡-** ለሕክምናዎ፣ ለክፍያዎ ወይም ለሌላ የጤና እንክብካቤ ክንውኖች አላማ ሲባል በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ወይም በሌሎች የጤና እንክብካቤ ተቋማት መካከል እና ከብዙ የጤና እንክብካቤ ተቋማት ጋር የኤሌክትሮኒክ የጤና መረጃዎን ምሥጢራዊ ልውውጥ ለማመቻቸት በጤና መረጃ ልውውጦች ላይ ልንሳተፍ እንችላለን። ይህ ማለት እያንዳንዳችን የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችዎን በተሻለ አያያዝ እና ቅንጅት ማቅረብ እንድንችል ስለእርስዎ የምንፈጥረውን ወይም የምናገኘውን መረጃ ከውጭ ተቋማት (እንደ ሆስፒታሎች፣ የዶክተሮች ቢሮዎች፣ ፋርማሲዎች ወይም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች) ጋር ልናጋራ እንችላለን ወይም ስለእርስዎ የሚፈጥሯቸውን ወይም ያገኙትን መረጃ (እንደ የመድኃኒት ታሪክ፣ የህክምና ታሪክ ወይም የኢንሹራንስ መረጃ) ልንቀበል እንችላለን። በተጨማሪም፣ ማንኛውንም የMedStar Health የጤና ተቋምን ከጎበኙ፣ የጤና እንክብካቤ መረጃዎ እርስዎን ለመንከባከብ፣ የጤና አገልግሎቶችዎን ለማስተባበር ወይም ለሌሎች ለተፈቀዱ ጉዳዮች ሊያውሉት ለሚችሉ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች እና ሰራተኞች ሊገኙ ይችላሉ።

ለታካሚዎቻችን የቼሰፒክ ክልላዊ የመረጃ ስርአት (CRISP) በምንሳተፍባቸው ሜሪላንድ እና ዋሺንግተን ዲሲ በማገልገል ላይ ያለ ክልላዊ የጤና መረጃ ልውውጥ ነው። ለህክምና፣ ለክፍያ፣ የጤና ክብካቤ ክንዋኔዎች ወይም ለምርምር አላማዎች በCRISP በኩል ስለ እርስዎ መረጃ ልናጋራ እንችላለን። በ877-952-7477 በመደወል ወይም የመርጦ መውጫ ቅጽ በመሙላትና በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በድረ ገጻቸው CrispHealth.org በኩል በማስገባት በCRISP በኩል ስላለው የጤና መረጃዎ "መርጠው-መውጣት" እንዲሁም እንዳይገኝ ማስቆም ይችላሉ። በህጉ በተፈቀደው መሰረት፣ ከCRISP መርጠው የሚወጡ ከሆነ እንኳን፣ ህዝባዊ የጤና ሪፖርት እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ንጥረ ነገሮች መረጃ፣ በሜሪላንድ በኪም የሚታዘዝ መድሃኒት ክትትል ፕሮግራም (PDMP) አካል ሆኖ፣ ለአገልግሎት አቅራቢዎች አሁንም በCRISP በኩል ይገኛል።

**የቀጠሮ ማስታወሻዎች እና የአገልግሎት መረጃ፡-** የቀጠሮ ማስታወሻዎችን ለማቅረብ ወይም የሕክምና አማራጮችን ወይም ሌሎች ጤና-ነክ አገልግሎቶችን ወይም እርስዎ ሊፈልጓቸው ስለሚችሉ ጥቅሞች ለእርስዎ ለማሳወቅ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**በእንክብካቤዎ ውስጥ ወይም ለእንክብካቤዎ ክፍያ የሚሳተፉ ግለሰቦች፡-** እንዳናደርግ ካልጠየቁን በስተቀር፣ በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች፣ ለምሳሌ እንደ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞችዎ የጤና መረጃዎን ልንሰጥ እንችላለን። የእንክብካቤዎ ክፍያን ለሚያግዝ ሰው መረጃዎን ልንሰጥ እንችላለን። መረጃዎን ለሌሎች የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች፣ የመንግስት ተወካዮች ወይም እንደ ቀይ መስቀል ያሉ የአደጋ እርዳታ ድርጅቶች፣ በድንገተኛ ወይም በአደጋ እርዳታ ሁኔታዎች ውስጥ ቤተሰብዎን ወይም ጓደኞችዎን ማግኘት ወይም የአደጋ እርዳታ ጥረቶችን ማስተባበር እንዲችሉ መረጃዎን ልናካፍል እንችላለን።

**የታካሚ የአድራሻ ማውጫዎች፡-** ስምዎን፣ በተቋሙ ውስጥ የሚገኙበትን አካባቢ እና አጠቃላይ ሁኔታዎን በስምዎ ለሚጠይቅ ለማንኛውም ሰው እንዲሰጥ በአድራሻ ማውጫ ውስጥ እንይዝ ይሆናል። ስምዎን ባያውቁትም እንኳን፣ ይህን መረጃ እና የሃይማኖት ወገንተኝነትዎን ለቀሳውስት ልንሰጥ እንችላለን። መረጃዎን ከአድራሻ ማውጫው ውጪ እንድናስቀምጥ ሊጠይቁን ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህን ካደረጉ፣ ጎብኚዎች እና አበባ ሻጮች ክፍልዎን ማግኘት እንደማይችሉ ማወቅ ይኖርብዎታል። ከአድራሻ ማውጫው ውጪ እንድናስቀምጥ ቢጠይቁን እንኳን፣ ለአደጋ እርዳታ ጥረቶች ወይም በታወጁ ድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን።

©2017 MedStar Health, Inc.

**የገቢ ማሰባሰብ ተግባራት፦** የጤና እንክብካቤ ተልዕኳችንን ለመደገፍ በስፋት በበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ እንመረኮዛለን። ለፕሮግራሞቻችን የገንዘብ መዋጮ ለማድረግ እድሉን ለእርስዎ ለማቅረብ እንዲያስችለን፣ የእንክብካቤዎ ቀናትን፣ የታከሙበትን ክፍል ስም እና ህክምና ያደረገልዎትን ሐኪም ስም፣ ስምዎን እና ሌላ የተገደበ መረጃን ጨምሮ እርስዎን ለማግኘት ልንጠቀምበት እንችላለን። የገቢ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎቻችንን ለማስተዳደር የጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲን ጨምሮ ከሶስተኛ አካል ጋር ልንተባበር እንችላለን። እኛ ወይም ማናቸውም ወኪሎቻችን ለገንዘብ ማሰባሰብ ወይም በጎ አድራጎት ተግባሮች እርስዎን ቢያናግሩ፣ ለወደፊቱ እርስዎን እንዳያነጋግሩ እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ ይነግርዎታል።

**ምርምር፦** የጤና መረጃዎን ግላዊነትን ለመጠበቅ የምርምር ፕሮፖዛልን እና የደረጃ መስፈርቶችን በገመገም፣ ከመደበኛ የምርምር ግምገማ ቦርዶቻችን ውስጥ በአንዱ ለተፈቀደ ምርምር የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። የምርምር ፕሮጀክት ለማካሄድ ለሚዘጋጅ አንድ ተመራማሪ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የአካል ክፍሎችና ህብረ ህዋሳት ልገሳ፦** ከአካል ክፍሎች ልገሳ፣ ከዓይን ወይም ከህብረ ህዋሳት ንቅለ ተከላ ወይም ከአካል ልገሳ ባንኮች ጋር በተያያዘ፣ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህን ተግባራት ለማመቻቸት፣ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የህዝብ ጤና እንቅስቃሴዎች፦** የጤና መረጃዎን ሕጋዊ ተግባራቶቻቸው በሽታን፣ ጉዳትን ወይም የአካል ጉዳትን መከላከል ወይም መቆጣጠርን ለሚያካትት የሕዝብ ጤና ወይም ሕጋዊ ባለስልጣናት አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ስለ ወሊድ፣ ስለሞት እና ስለተለያዩ በሽታዎች ለመንግሥት ኤጀንሲዎች የተወሰኑ መረጃዎችን ሪፖርት ማድረግ አለብን። በህግ በተፈቀደው መሰረት ለአስከሬን መርማሪዎች፣ ለሕክምና መርማሪዎች እና ለቀብር አስፈፃሚዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የጤና መረጃ አሳልፈን ልንሰጣቸው እንችላለን። በመድሃኒቶች ላይ ያሉ አጸፋዊ ምላሾችን፣ በምርቶች ላይ ያሉ ችግሮችን ሪፖርት ለማድረግ ወይም ሰዎች እየተጠቀሙባቸው ሊሆኑ የሚችሉ ምርቶች ከገበያው ተመላሽ መደረግን ለማስታወቅ የጤና መረጃን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ለበሽታ ለተጋለጠ ወይም ለበሽታ የመጋለጥ ወይም የማሰራጨት አደጋ ላይ ሊሆን ለሚችል ግለሰብ ለማስታወቅ የጤና መረጃን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**ለጤና እና ደህንነት አስጊ አደጋ፦** ለጤናዎ እና ለደህንነትዎ ወይም ለህዝብ ወይም ለሌላ ሰው ጤንነት እና ደህንነት አደገኛ ሁኔታን ለመግታት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። እንደ ሕግ አስፈፃሚ ወይም የመንግስት ባለስልጣናት ያሉ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ስጋቶችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ለሚችል ሰው ብቻ የጤና መረጃን አሳልፈን እንሰጣለን።

**በህግ፣ በህጋዊ ሂደቶች፣** በጤና ቁጥጥር ተግባራት እና በህግ ማስከበር የሚፈለጉ፦ በፌዴራል፣ በስቴትና በሌሎች ህጎች ይፋ እንድናወጣ ከተጠየቅን የጤና መረጃዎን አሳልፈን እንሰጣለን። ለምሳሌ፣ የብዝበዛ፣ የቸልተኝነት ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችን እንዲሁም የተኩስ እና ሌሎች ቁስሎች ያለባቸው ታካሚዎችን ሪፖርት ማድረግ ሊፈለግብን ይችላል። የፍርድ ቤት መጥሪያ፣ የግኝት ጥያቄ፣ ዋራንት፣ የመያዣ ማዘዣዎች፣ ወይም ሌላ ሕጋዊ ሂደትን የመሳሰሉ በህግ ወይም በአስተዳደራዊ ሂደቶች ውስጥ ሲታዘዙ የጤና መረጃዎን አሳልፈን እንሰጣለን። ተጠርጣሪዎችን፣ የሸሹ ሰዎችን፣ ምስክሮችን፣ የወንጀል ሰለባዎችን ወይም የጠፉ ሰዎችን ለመለየት ወይም ያሉበትን ለማወቅ ለህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን የጤና መረጃ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። በወንጀል ድርጊት ወይም በተቋማችን ውስጥ ተከስቶ ሊሆን የሚችል የወንጀል ተግባር ውጤት ሊሆን ይችላል ብለን ስለምናምነው ሞት፣ ለህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን የጤና መረጃ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። በሕግ ለተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች ማለትም እንደ ኦዲቶች፣ ምርመራዎች፣ ፍተሻዎች እና ፍቃድ መስጠትን ለመሳሰሉ የጤና መረጃን ለጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

©2017 MedStar Health, Inc.

**የተለዩ የመንግስት ተግባራት፡-** በጦር ኃይሎች ውስጥ ወይም አርበኛ ከሆኑ በአዛዥ በባለስልጣናት በሚጠየቀው መሰረት የጤና መረጃዎን አሳልፈን እንሰጣለን። የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንትን መጠበቅ ወይም የተፈቀዱ የደህንነት ክንውኖችን ማከናወንን ለመሳሰሉ የሀገራዊ ደህንነት ዓላማዎች፣ ለተፈቀደላቸው የፌደራል ባለስልጣኖች የጤና መረጃን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ለውጪ አገልግሎት የሕክምና ብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን ለመወሰን የጤና መረጃን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የማረሚያ ተቋማት፡-** የማረሚያ ተቋም እስረኛ ወይም በህግ አስከባሪ ባለስልጣን ቁጥጥር ስር ከሆኑ የጤና መረጃዎን ለማረሚያ ተቋሙ ወይም ለሕግ አስፈፃሚ ባለስልጣኑ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን። ለጤንነትዎ እና ለደህንነትዎ፣ ለሌሎች ጤና እና ደህንነት ወይም ለማረሚያ ተቋሙ ደህንነት እና ጥንቃቄ ሲባል የጤና መረጃዎን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የሰራተኞች ካሳ፡-** ተፈጻሚ በሆኑ የሰራተኛ ካሳ እና ተመሳሳይ ህጎች እንደተፈለገ የጤና መረጃዎን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

**የጤና እቅድ፡-** MedStar Health እንደ አንድ የጤና እቅድ ሲከውን፣ ለጋራ እቅድ ሽፋን ብቁነትን ለመወሰን ዓላማዎች የዘረ-መል መረጃዎን አንጠቀምም ወይም አሳልፈን አንሰጥም።

**የእርስዎ የፅሑፍ ፍቃድ**፡- በዚህ ማስታወቂያ ወይም እኛን በሚገዙት ሕጎች ያልተሸፈኑ የጤና መረጃዎችዎ ሌሎች አገልግሎቶች እና ይፋ መውጣቶች በእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ብቻ ይደረጋሉ። እነዚህም የጤና መረጃዎን ሽያጭ፣ የጤና መረጃዎን ለግብይት አላማዎች መጠቀምን እና የተወሰኑ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች ይፋ መደረግን ያካትታሉ። በማንኛውም ሰዓት በጽሁፍ ፈቃድዎን መሻር ይችላሉ እና በእርስዎ ፈቃድ ለተሸፈኑ ምክንያቶች የወደፊቱን የጤና መረጃዎን መጠቀም እና ይፋ መውጣቶች እናቋርጣለን። በእርስዎ ፈቃድ የተደረጉ ማናቸውንም የመረጃ ይፋ መውጣቶች ወደኋላ መመለስ አንችልም፣ እና ለእርስዎ ያቀረብናቸውን እንክብካቤዎች መዝገቦች ይዘን መቆየት ይፈለግብናል።

## <u>የጤና መረጃዎን በተመለከተ የግላዊነት መብቶችዎ</u>

### የዚህን የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ ግልባጭ የማግኘት መብት

የአሁኑ ማስታወቂያችንን ቅጂ በተቋማታችን እና ድረገጻችን ላይ እንለጥፈዋለን፣ **MedStarHealth.org.** የአሁኑ ማስታወቂያችንን ቅጂ በምዝገባ ቦታዎች ላይ በተጠየቀ ጊዜ የሚገኝ ይሆናል። አሁን ያለንን የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ ቅጂ ለመጠየቅ፣ በ **410-772-6606** ይደውሉ።

### የጤና መዝገብዎን የማየት እና የመቅዳት መብት

የሕክምና መዝገብዎን ወይም የሂሳብ አከፋፈል ሪኮርድዎን የማየት እና አንድ ቅጂ የመቀበል መብት አለዎት። ይህን ለማድረግ፣ ህክምና ያገኙበትን ተቋም ወይም የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮን ያነጋግሩ። ጥያቄዎን በጽሁፍ እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ።

የዚህን መረጃ ኤሌክትሮኒክ ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ፣ እና በተጠየቀው ቅርጸት በቀላሉ ሊባዛ የሚችል ከሆነ በኤሌክትሮኒክ መልክ እና ቅርጸት ወደ መረጃ መድረስን እናቀርባለን። ካልሆነ ግን፣ ጉዳዩን ከእርስዎ ጋር እንወያይበት እና ጥያቄው በሚጠየቅበት ጊዜ ላይ ባለው መረጃ እና ችሎታችን ላይ በመመርኮዝ፣ በጋራ በምንስማማበት በሚነበብ በኤሌክትሮኒክ ቅጽ እና ቅርጸት ላይ እናቀርባለን።በተጨማሪም የርስዎን የጽሁፍ ጥያቄ ፣በተፈረመ እና በጽሁፍ አድርጎ በጽሑፍ የተወከለውን ግለሰብ እና የተጠየቀውን መረጃ መላኪያ አድራሻ በግልጽ በሚለይበት ሁኔታ፣ የጤና መረጃዎን በቀጥታ ለሚልኩት ሰው እንዲላክልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

©2017 MedStar Health, Inc.

የጤና መዝገብዎን ቅጂ ከፈለጉ፣ በህግ እንደተፈቀደው መረጃዎን ለመቅዳት ወይም ለመላክ (እና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው ጥያቄው በተንቀሳቃሽ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ላይ መረጃውን ማቅረብ ከሆነ) ክፍያ ሊከፈል ይችላል።

በአብዛኛው የጤና መዝገብዎን ግልባጭ በ 30 ቀናት ውስጥ እንሰጥዎታለን። በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ጥያቄዎን ልንከለክል እንችላለን። እንደዚያ ካደረግን፣ ለክልከላችን ምክንያቶቹን በጽሑፍ እናሳውቅዎታለን እንዲሁም ክልከላው በድጋሚ እንዲታይልዎት የመጠየቅ መብትዎን እንገልጻለን።

**የጤና መዝገብዎን የማዘመን መብት**

ከጤና መዝገብዎ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ መረጃ ጠፍቷል ብለው ካመኑ፣ በመዝገብዎ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አለዎት። ጥያቄዎ በጽሑፍ መሆን ያለበት ሲሆን ለጥያቄዎ ምክንያቱን ማካተት አለበት።ጥያቄዎን ለማስገባት፣ ህክምና ያገኙበትን ተቋም ወይም የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮን ያነጋግሩ። ጥያቄዎን በአብዛኛው በ 60 ቀናት ውስጥ ለማሟላት እንጥራለን። መረጃው ትክክለኛ እና የተሟላ እንደሆነ ካመንን፣ የሚስተካከለው መረጃ በእኛ ያልተፈጠረ ከሆነ፣ ወይም መረጃው በህጉ እንዲታዩ እና እንዲቀዱ በተፈቀዱ ሪኮርዶች ውስጥ ከሌለ ሪከርድዎን የማሻሻል ጥያቄዎን ልንከለክል እንችላለን። ጥያቄዎን ከከለከልን በአብዛኛው በ 60 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያውቁት ይደረጋል። ማሻሻያዎን ብንቀበል እንኳን፣ በመዝገብዎ ውስጥ ያለን ማንኛውንም መረጃ አንሰርዝም።

**ይፋ ያወጣናቸውን ዝርዝሮች የማግኘት መብት**

ከጤና መረጃዎ ይፋ ያወጣናቸውን ዝርዝሮች የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህ ዝርዝር ለህክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ክንውኖች ይፋ የተደረጉ መረጃዎችን እና የተወሰኑ የይፋ ማውጣት ልዩ ሁኔታዎች ማካተት አይጠበቅበትም። ጥያቄዎ በጽሑፍ መሆን ያለበት ሲሆን ዝርዝሩን የሚፈልጉበትን መንገድ (ለምሳሌ፣ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒካዊ) ማሳየት አለበት። ይፋ የወጡ ዝችዝሮችን ለመጠየቅ፣ ህክምና ያገኙበትን ተቋም ወይም የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮን ያነጋግሩ። በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የሚጠይቁት የመጀመሪያው ዝርዝር ነጻ ነው። በህጉ በተፈቀደው መሰረት፣ ለተጨማሪ ዝርዝሮች ክፍያ ልናስከፍል እንችላለን።

**በተወሰኑ ይፋ ማውጣቶች ላይ ገደብ እንዲጣል የመጠየቅ መብት**

ለሕክምናዎ፣ ለክፍያዎ እና ለጤና እንክብካቤ ክንውኖች እና በእርስዎ እንክብካቤ ላይ ወይም ለእንክብካቤዎ ለሚከፍሉት ክፍያ ተሳታፊ ለሆኑ በእርስዎ የተለዩ የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞችዎ የጤና መረጃዎ እጠቃቀማችን እና ይፋ አደራረጋችን ላይ ገደብ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አለዎት። ከጥያቄዎ ጋር መስማማት አይጠበቅብንም፣ እናም መስማማት የማንችል ከሆነ እናሳውቅዎታለን። ጥያቄዎ በጽሑፍ መሆን አለበት፣ እና (1) እርስዎ ምን አይነት መረጃ መወሰን እንደሚፈልጉ መግለጽ አለበት፣ (2) የኛን አጠቃቀም፣ ይፋ ማድረግ ወይም ሁለቱንም ለመገደብ ነው የሚፈልጉት፣ እና (3) ገደቡ በማን ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ነው የሚፈልጉት። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ለኢንሹራንስ ኩባንያዎ የይገባኛል ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ ለጤና እንክብካቤ ንጥል ወይም አገልግሎት ከኪስዎ መክፈልን ሊመርጡ ይችላሉ። እርስዎ ወይም ሌላ ሰው በእርስዎ ምትክ ለህክምና ወይም ለአገልግሎት ሙሉ በሙሉ ከኪሳቸው ከከፈሉ፣ የጤና መረጃዎን ለጤና እቅድ ወይም ለኢንሹራንስ ኩባንያዎ እንዳናስገባ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህንን ገደብ ለመጠየቅ፣ ከህክምናው ወይም ከአገልግሎቱ አስቀድመው ጥያቄዎን በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርቦታል። በጥያቄዎት ውስጥ (1) ምን ዓይነት መረጃን ለመገደብ እንደሚፈልጉ እና (2) እገዳው ተፈጻሚነት የሚኖረው የትኛው የጤና እቅድ ላይ እንደሆነ ሊነግሩን ይገባል።

©2017 MedStar Health, Inc.

**የጥሰት ማሳወቂያ መብት**

ያልተጠበቀ የሕክምና መረጃዎት ጥሰት ካለ፣ በ HIPAA መሠረት ወይም በህግ በተደነገገው መሠረት እንዲያውቁት የመደረግ መብት አለዎት። ከተጠየቀ፣ ይህ ማሳወቂያ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሊቀርብልዎ ይችላል።

**ተወካይ የመምረጥ መብት**

በእርስዎ ምትክ የሆነ እርምጃ የሚወስድ ሰው የመምረጥ መብት አለዎት። ለአንድ ሰው የሕክምና ውክልና የሰጡ ከሆነ ወይም የሆነ ሰው ህጋዊ ሞግዚትዎ ከሆነ፣ ያ ሰው የእርስዎን መብቶች ሊጠቀምና እና የእርስዎ የጤና መረጃ የተመለከቱ ምርጫዎች ማድረግ ይችላል። የምትመርጡት ሰው ይህ ስልጣን ያለው መሆኑን እና ማንኛውም እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ለእርስዎ እርምጃ እንደሚወስድ ለማረጋገጥ እንጥራለን።

**የህክምና መረጃዎን እንዴት እንደሚቀበሉ የመምረጥ መብት**

በደብዳቤ ወይም በፋክስ፣ በቤት አድራሻ ወይም በፖስታ ሳጥን የመሳሰሉ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ከእርስዎ ጋር በተወሰነ መንገድ እንድንገናኝ የመጠየቅ መብት አለዎት። ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የምንችል ከሆነ፣ የእርስዎን ጥያቄዎ ለማክበር እንሞክራለን። ጥያቄዎ በጽሑፍ መሆን አለበት፣ እና እንዴት እና የት መገናኘት እንደሚፈልጉ መግለጽ አለበት።ጥያቄ ለማስገባት፣ እባክዎን ህክምና ያገኙበትን ተቋም ወይም የ **MedStar Health** የግላዊነት ቢሮን ያነጋግሩ።

**<u>ተጠሪ</u>**

የግላዊነት መብቶችዎ ተጥሰዋል ብለው ካሙኑ፣ ቅሬታዎን በ MedStar Health Privacy Office ወይም በ Department of Health and Human Services በኩል ጽፈው ማመልከት ወይም መደወል ይችላሉ (እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን የመገኛ መረጃ ይመልከቱ)።ስለ ግላዊነት አሰራሮቻችን ቅሬታ ካስገቡ በእርስዎ ላይ ምንም የበቀል እርምጃ አንወስድም።

Privacy Officer MedStar Health, Inc.
10980 Grantchester Way, Columbia, MD 21044
ስልክ 410-772-6606
**PrivacyOfficer@MedStar.net**

U.S. Department of Health and Human Services Office for Civil Rights
200 Independence Avenue, S.W., Washington, D.C. 20201,
1-877-696-6775 (toll free)
**HHS.gov/OCR/Privacy/HIPAA/Complaints.**

ይህን ማስታወቂያ በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ወይም የግላዊነት መብቶችዎን ለመውሰድ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ህክምና ያገኙበትን ተቋም ያነጋግሩ, ወይም የ MedStar የግላዊነት ቢሮን ያነጋግሩ.

**MedStar Health** complies with applicable federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability or sex.

注意：如果您使用繁體中文，您可以免費獲得語言援助服務。請致電 **877-772-6505**.

ATTENTION: Si vous parlez français, des services d'aide linguistique vous sont proposés gratuitement. Appelez le **877-772-6505**.

주의: 한국어를 사용하시는 경우, 언어 지원 서비스를 무료로 이용하실 수 있습니다. **877-772-6505** 번으로 전화해 주십시오.

ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al **877-772-6505**.

©2017 MedStar Health, Inc.

## <u>በዚህ የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ ላይ ለውጦች</u>

ይህንን ማስታወቂያ የመቀየር መብት አለን ቀደም ብለን ስለ እርስዎ ባለን መረጃ እና ለወደፊቱ በምናገኘው ማንኛውም መረጃ ላይ የተሻሻለውን ማስታወቂያ ተግባራዊ የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። የአሁኑን ማስታወቂያ ቅጂ በእያንዳንዱ የ MedStar Health ተቋም እና በድረ ገጻችን እናወጣዋለን። በተጨማሪም፣ በሆስፒታል ውስጥ ለህክምና ወይም ለጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንደ ውስጥ ታካሚ ወይም የውጭ ታካሚ ሲገቡ ወይም ሲመዘገቡ በወቅቱ በስራ ላይ ያለውን የማስታወቅያችንን ቅጂ እንሰጥዎታለን።

**El Aviso sobre Prácticas de Privacidad está disponible en español.**
개인 정보 보호 정책 관행의 공지 사항 한글로 사용할 수있습니다.
**مذكرة الخصوصية متاح باللغة العربية.**
通知隐私做法是可以在简体中文。
**Các thông báo về việc bảo mật Thực tiễn hiện có sẵn tại Việt Nam**
Уведомление о конфиденциальности доступна на русском языке.

*የግርጌ ማስታወሻ፦ MedStar Health Inc. በኮሎምቢያ፣ ሜሪላንድ ውስጥ የሚገኝ ለትርፍ ያልተቋቋመ ሜሪላንድ እና ዋሽንግተን ዲሲን በማገልገል ላይ ያለ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የጤና እንክብካቤ ማህበር ነው። የጤና ስርዓቱ ከተለያዩ ታዋቂ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች እና ሌሎች የተለያዩ የጤና እንክብካቤ ተቋማት የተገነባ ነው። እነዚህ ተቋማት እርስ በእርሳቸው በየፊናቸው እና እንደ ተናጠል አሠሪዎች የሚሰሩ ቢሆንም ለጋራ ተልዕኮ እና እሴቶችም ይሠራሉ። የ MedStar ተልዕኮዎቻችን ታካሚዎቻችንን፣ ለእነርሱ እና ለማህበረሰቦቻችን የሚንከባከቡትን ማገልገል ነው፣ እና ራዕያችን ሰዎችን በመንከባከብ እና ጤናን በማሻሻል የታመነ መሪ መሆን ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት በመስራት ውስጥ፣ የግላዊነት ፖሊሲዎቹን ተግባራዊ ማድረግ እና ለሠራተኛው ጥሰቶች ተገቢ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ወይም ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ መቻሉ እያንዳንዱ የMedStar አካል ኃላፊነት ነው። እባክዎን ለዚህ የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ ዓላማዎች የ MedStar Health እናት ኩባንያ እና ሁሉም ቅርንጫፎች በጋራ "MedStar Health" ተብለው እንደሚጠሩ ያስተውሉ። ለግላዊነት ዓላማዎች ብቻ፣ የMedStar Health በ 45 CFR §164.504 (d) (1) በተገለፀው መሰረት እንደ ተዛማጅ ሽፋን ያለው ተቋም የተደራጀው፣ ከህግ አንጻር የተለያዩ ተባባሪዎች እራሳቸውን እንደ አንድ የተሸፈነ አካል አድርገው ሊጠቁሙ ይችላሉ።*

©2013 MedStar Health, Inc.